

# ጋዜጣዊ መግለጫ
# የአሜሪካ ኤምባሲ
# አዲስ አበባ

*2017/13*

ለተጨማሪ መረጃ በ011-130-7033 ይደዉሉ
http://ethiopia.usembassy.gov

---

## የአሜሪካ መንግሥት ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት በደቡብ/ብ/ብ/ሕ ክልል የጤና ማዕከል ከፈተ

***አዲስ የተገነባው ማዕከል ከ25,000 በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል***

***ፍንጫዋ፤ ደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል፤ ኢትዮጵያ፤ ግንቦት 18፤ 2008፤-*** የአሜሪካ መንግሥት ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) አዲስ ያስገነባውንና በደቡብ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል በፍንጫዋ እና አካባቢው የሚገኙ ከ25,000 በላይ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የጤና ማዕከል ለክልሉ መንግሥት ጤና ቢሮ ዛሬ አስረከበ፡፡

የልማት ድርጅቱ በኢትዮጵያ በሚተገብረው የጤና መሠረተ ልማት መርሐ-ግብር አማካይነት በዋና ዋና ክልሎች የጤና መሠረተ ልማቶችን በመገንባት ነፍሰጡር ሴቶች በሰለጠነ ባለሙያ እንዲገላገሉ እና ከኤች አይ ቪ ጋር የሚኖሩ ወገኖች የፀረ ኤች አይ ቪ  መድሃኒት እንዲያገኙ በማድረግ ሀገሪቱ የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት የምታደርገውን ጥረት ይደግፋል፡፡

በጤና ማዕከሉ ርክክብ ሥነሥርዓት ላይ ንግግር ያደረጉት የአሜሪካ መንግሥት ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት ተወካይ ሶፊያ ብርዌር የአካባቢውን ማኅበረሰብ “እንኳን ደስ ያላችሁ” ካሉ በኋላ “የጤና ማዕከሉ እንደ ክትባት፤ የወሊድ አገልግሎት፤ የኤች አይ ቪ ክብካቤ እና ህክምና አገልግሎትን ጨምሮ ሌሎችን ህይወት አድን እና አስፈላጊ የጤና አገልግሎቶችን ይሰጣል” ብለዋል፡፡

የልማት ድርጅቱ በአሜሪካ ፕሬዚዳንት የአስቸኳይ ዕቅድ ለኤድስ ድጋፍ (PEPFAR) የገንዘብ ድጋፍ በሚተገበረው የጤና መሠረተ ልማት መርሐ-ግብሩ አማካይነት፤ 10 የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖችን እና አምስት የጤና ማዕከላትን ግንባታ እንዲሁም ሌሎች 10 የጤና ማዕከላት እድሳት በማከናወን ድጋፍ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም፤ የአሜሪካ መንግሥት ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) በአዲስ አበባ እጅግ ዘመናዊ የብሔራዊ የደም ባንክ እየገነባ ሲሆን፤ በአማራና ደቡብ ክልሎች ግንባታቸው የተጠናቀቁ ስድስት የጤና ማዕከላትን ጨምሮ 17 ተመሳሳይ ማዕከላትን ግንባታ እያከናወነ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ የፕሬዚዳንት የአስቸኳይ ዕቅድ ለኤድስ ድጋፍ (PEPFAR) የረዥም ጊዜ ውጥን አካል እንደመሆኗ፤ በአሜሪካ መንግሥት ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት፤ በአሜሪካ መንግሥት የበሽታዎች ቁጥጥርና መከላከል ማዕከል (ሲዲሲ)፤የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር መሥርያ ቤት፤ የሰላም ጓድ እና የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የስነ-ህዝብ፤ስደተኞች እና ፍልሰት ቢሮ የሚተገበሩ ዘርፍ-አቀፍ የኤች አይ ቪ መርሐ-ግብሮች ተጠቃሚ ናት፡፡ የአሜሪካ መንግሥት ከ1997 ዓ.ም. ወዲህ በፕሬዚዳንት የአስቸኳይ ዕቅድ ለኤድስ ድጋፍ (PEPFAR) በኩል ባደረገው ድጋፍ፤ ኢትዮጵያ አዳዲስ በኤድስ የሚያዙ ሰዎችን ቁጥር እና ከኤድስ ጋር የተያያዘ ሞትን በትንሹ በ50 በመቶ እንድትቀንስ አስችሏታል፡፡

###

*For more information, see https://www.usaid.gov/ethiopia*